የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.25
ADDIS ABABA 4th February, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፫/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በእስራኤል መንግስት መካከል የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ……………………………………..……..ገጽ ፲ሺ፱፻፸፰

## Content

Proclamation No.1103/2019

The Air Service Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Israel Ratification Proclamation --…..Page 10978

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፫/፪ሺ፲፩

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በእስራኤል መንግስት መካከል የተፈረመው የአየር አገልግሎት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በእስራኤል መንግስት መካከል የተፈረመው የአየር አገልግሎት ስምምነት መስከረም ፬ ቀን ፪ሺ.፬ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሳስ ፳፭ ቀን ፪ሺ.፲፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በእስራኤል መንግስት መካከል የተደረገ የአየር አገልግሎት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፩፻፫/፪ሺ.፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1103/2019

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AIR SERVICE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE STATE OF ISRAEL**

**WHEREAS,** the Air Service Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Israel was signed in Addis Ababa on the 15th day of September, 2011;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 3rd day of January, 2019;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows.

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "the Air Service Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Israel Ratification Proclamation No.1103/2019."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

www.chilot.me

**፪. ስምምነቱ ስለመፅደቁ**

፩. በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በእስራኤል መንግስት መካከል መስከረም ፬ ቀን ፪ሺ.፬ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የአየር አገልግሎት ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፪. በስምምነት ሰነዱ አንቀፅ 23 (7) የተመለከተው "በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተሰጠው ውሳኔ" የሚለው "በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) የተሰጠው ውሳኔ" በሚል ታርሞ ፀድቋል፡፡

**፫. አስፈፃሚ አካል**

ይህ ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን ለኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሺን ባለስልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፪ሺ.፲፩ ዓ.ም.**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**2. Ratification of the Agreement**

1. The Air Service Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Israel signed in Addis Ababa on the 15th day of September, 2011 is hereby ratified.
2. In Article 23(7) of the Agreement the statement "the decision given under paragraph (2) of this Article" is corrected and ratified as "the decision given under Sub Article (6) of this Article."

**3. Implementing Organ**

The Ethiopian Civil Aviation Authority is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 4th day of February, 2019.**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me